1.6 ኪሎ ሜትር የዳሌ ስፋት ባላቸው ድንግል ሴቶች የተሞላው የእስልምናው ጀነት

ይህን ፅሁፍ እንድለጥፍ ምክንያት የሆነኝ ከደቂቃዎች በፊት አንድ የኔታ የተባለው የዩቱብ ቻናል ላይ አንድ አብዱል የተናገረውን ቪዲዮ ስመለከት ነው። እርሱ እንደሚለውም

''...እኔ በግሌ እምነቴን እንደሚከተል ሰው ስነግርሽ የትኛውም ክርስቲያን ጀነት ይገባል የሚል እምነት የለኝም..." ነበር ያለው።

ማንም ሰው የምከተለው እምነት ትክክል ነው። በአንፃሩም የሌላው እምነት ትክክል አይደለም ብሎ እንደማመኑ የዚህም ሰው ይህ አመለካከት በእርግጥ ከዚህ እምነቱ የመነጨ እንደመሆኑ ትክክል ነው እላለሁ።

ይሁንና ግን ደግሞ እዚህ ጋር ይህ ሰው ጀነት ስለሚለው ቦታ የተወሰነ ግለቱን ወደድኩ። በዚህም መሠረት በመጀመሪያ አንባቢያን እንዲያውቁት የምፈልገው ቁልፍ ነጥብ በእስልምና በሚታወቀው ጀነትና በክርስትና የሚታወቀው ጀነት መካከል የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት ያለ መሆኑን ነው።

አንባቢያን እንዲያሰምሩበት የምፈልገውም ነገር ልጁ(የኔታ ላይ የቀረበው) ብቻም ሳይሆን እኛም ክርስቲያኖች ብንሆን የእስልምናውን ጀነት እንደማንገባና መግባትም እንደማንፈልግ ነው።

እንዴ ለምን? የሚል ጥያቄ ከተነሳ ደግሞ እነሆ ምክንያቴን ከዚህ በታች ከሳሂህ ኢማን 'የእስልምናው ጀነት፦ ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ!' ከሚለው መፅሀፍ ቀንጭቤ አቅርቤዋለሁና የቀረበውን ጽሁፍ አንብባችሁ ፍረዱኝ ማለት እወዳለሁ(ሙሉ መፅሀፉን ከJoshua evangelical army ገጽ ልታገኙት ትችላላችሁ አልያም ኢሜይላችሁን በውስጥ መስመር ዱቅ አርጉልኝ ከተወሰኑ ቀናት በኻላ እልክላችኻለሁ)

".....ሚስት ተብየዎቹ አዲስ ፍጥረታት ናቸው። ሱረቱል አል-ዋቂያህ 56 ፥ 35 እንዲህ ይላል፦ 'እኛ አዲስ ፍጥረት አድርገን (ለእነርሱ) ፈጠርናቸው።'

በጣም የገረመኝ ደግሞ የወርቅ ፍልቃቂ የመሰሉ እናት፣ ልጆች፣ እህቶች፣ አክስቶች ሚስት ያሉት ሰው በጣም የሚያስጠሉና ዘግናኝ እንግዳ ፍጥረት ሴት ተስፋ ማድረጉ ነው።

"አቡ ሁሬይራ እንዳወራው አቡ ቃሲም እንዲህ አልተናገሩምን?፦ ‘ከገነት ገቢዎች የመጀመሪያው ቡድን ልክ እንደ ሙሉ ጨረቃ ይመስላል፤ የሚቀጥለው ቡድን ደግሞ በሰማይ ላይ እንደምታንጸባርቅ ኮከብ ይመስላል። ከእነርሱ እያንዳንዳቸው የአጥንታቸው መቅኔ በሥጋቸው ውስጥ የሚታይ ሁለት ሁለት ሚስቶችን ያገባሉ፤ በገነት ያላገባ አይኖርም።'" (Tafsir Ibn kathir vol 9, page 401)

አዲስ ፍጥረት ለምን? የሙስሊሙ እናት፣ እህት፣ ልጅ፣ ሚስት የትሄደው ነው አዲስ ፍጥረት ያስፈለገው? እዚህ ያሉት ሴቶችማ በተለያየ ምክንያት እዛ የሉማ! ምናልባት የባሎቻቸውን ውለታ ዘንግተውም ሊሆን ይችላል ወደ ገሃነም የተጣሉት። እኔ አይደለሁም ይህን ያልኩት፤ የነብያቱ መደምደሚያ፣ የእዝነቱ ነቢይ ናቸው። ሳሂህ አል-ቡኻሪ ቅጽ 1፣ 2 ፥ 28 ይህን ብሏል

"በኢብን አባስ የተነገረ ነው፤ ነቢዩ እንዲህ አሉ፦ ‘ገሃነመ እሳትን አየሁ፣ አብዛኞቹ ወደዛው ገቢዎች ደግሞ ውለታ ቢስ የሆኑ ሴቶች ናቸው።’ እንዲህ ሲሉም ጠየቁ፦ ‘በአላህ ነው የካዱት?’ (ወይም ለአላህ ነው ውለታቢስ የሆኑት?) ሲመልሱም፦ ‘ውለታ ቢስነታቸው ለባሎቻቸው ነው፤ ላደረጉላቸው መልካም እና ለዋሉላቸው ውለታ ነው ውለታ ቢስ የሆኑት። ከእነርሱ ላንዷ ሁልጊዜ መልካም ታደርጉላትና የማትወደውን ነገር በእናንተ ላይ ስታይ ከእንተ ምንም ዓይነት መልካም ነገር አላገኘሁም ትላለች።"

ተስፋ አላቸው ቢባል እንኳን አንድን ወንድ ከስንት ሴቶች ጋር ተጋርተው እንደሚኖሩ ተመልከቱ። ካላገባች 1/4000 አግብታ የፈታች ከሆነች ደግሞ 1/8000 ይዘገንናል! ይህ ነው የሙስሊም ሴት ተስፋ፦

"አንድ ሰው ነቢዩን እንዲህ ሲል ጠየቀ፦ የአላህ ነቢይ ሆይ የገነት ነዋሪዎች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይፈጽማሉን? ከእነርሱ መካከል የሆነ እያንዳንዱ ሰው ከእናንተ የሰባት ሰዎችን ያህል የወሲብ ጥንካሬ ይሰጠዋል። ነቢዩም እንዲህ አሉ፦ የገነት ነዋሪዎች 500 የገነት

ሴቶች፣ 4000 ያላገቡ ሴቶችና 8000 አግብተው የፈቱ ሴቶች ይኖሩታል።" (Ihya Ulum-Id-Din, vol 4, page 430.)

እነዚህን የወርቅ ፍልቃቂ የመሰሉ እናቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውን፣ እህቶቻቸውን፣ አክስቶቻቸውን ሚስቶቻቸውን የሚያቀልና የሚያዋርድ ተስፋን ነው ተስፋ ብለው ተቀብለው ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉት? አንተ ሙስሊም ወንድሜ ሆይ! እነዚህ ውድ ቤተሰቦችህ በእንዲህ አይነት ውርደት ዘላለም እንደሚኖሩ ስታስብ ምን ይሰማሃል? እውን አላህ ፍትሀዊ አምላክ ነው ይላል ልብህ? ሴቷስ ይህ እንደሆን ተስፋዋ ሲነገራት እንዴት ብላ አልሀምዱሊላሂ አለች?

ሙስናድ አቢ ሁሬይራ ሙስናድ አህመድ ኢብን ሐምባሊ ቁጥር 10511 ደግሞ ይህን አስነብቧል፦
“የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፦ ‘በገነት የሰው ዝቅተኛው ስልጣን ሰባት ደረጃ አለው፤ ስድስተኛ ደረጃ ላይ ያለውና ከእርሱ ከፍ ብሎ ሰባተኛ ደረጃ ላይ ያለ ሰው 300 አገልጋዮች አሉት፤ በየቀኑ 300 የወርቅ ትሪ ምግብ ይቀርብለታል። በያንዳንዱ ትሪ ላይ ያለ ምግብ አይነት አንዱ ከሌላው ይለያል፤ የምግቡም ጥፍጥና ከጅምሩ እስከ መጨረሻ አንድ ነው። እንዲህም ይላል፦ "ጌታየ ሆይ! ለገነት ሰዎች እንድመግብና የሚጠጡት እንድሰጣቸው ስልጣን ብትሰጠኝ ከእኔ ምግብ ቅንጣት ያህል አይቀንስም፤" ደግሞም በምድር ከነበሩት ሚስቶቹ የተለዩ 72 ልጃገረድ ሚስቶች ይኖሩታል፤ የእያንዳንዷ ድንግል የመቀመጫ ስፋት የምድር አንድ ማይል (1.6 ኪ.ሜ) ያህል ነው'።”

ባለ 30 ሜትር ቁመቱ 7.5 ሜትር ስፋት ያለው ከሆነ ባለ 1.6 ኪ.ሜ የመቀመጫ ስፋቷ አስፈሪ ፍጡር ቁመቷ ስንት ሊሆን ይችላል ብላችሁ ብታሰሉ ምን እንደምታክል ትደርሱበታላችሁ። ንገረን ካላችሁም 13 ኪ.ሜ አካባቢ ይሆናል። እንግዲህ 30 ሜትር አቡ ሀይደር በ 13 ኪ.ሜ ስም የለሽ ሚስቱ ላይ ምን ሊያደርግ ይችላል? ----አጃኢብ ነው!"